# <u>ለቱሪዝምና ለባህል ልውውጥ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 54/2003</u>

በአዋጅ ቁጥር 622/01 አንቀፅ 54 እና 55 ዕቃዎች ለባህልና ለቱሪዝምአገልግሎት በጊዜያዊነት ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉና በሚገቡበትም ጊዜ ዋስትና ማስያዝ አስፈላጊ መሆኑ የተደነገገ ቢሆንም የሚያዘው የዋስትና ዓይነት እነዚህ ዕቃዎች ወደ አገር ውስጥ ገብተው የሚቆዩበትን ጊዜ፤ የሚያስገቡት ሰዎች የሚኖራቸውን መብትና ግዴታ የሚወስን ዝርዝር አፈፃፀም በማውጣት የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት በማስፈለጉ፤

እንዲሁም በሚገቡት ዕቃዎችና በአስገቢዎቹ ላይ ውጤታማ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ግልፅና ወጥ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 622/01 አንቀፅ 112/2 መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "ለቱሪዝምና ለባህል ልውውጥ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 54/2003 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

1. **"ቱሪስት"** ማለት ወደ ኢትዮጵያ ግዛት መግባት የሚያስችል ፈቃድ/ቪዛ ያለው ወይም የኢትዮጵያ መንግሥት ባደረገው ስምምነት ወይም በህግ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ለመግባት የሚፈቀድለት ሆኖ ለጉብኝት ወይም ለባህል ልውውጥ ወይም አገር ውስጥ በሚዘጋጁ የባህል ፌስቲቫሎች ላይ ለመሳተፍ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ሰው ነው፡፡

2. **"ዕቃ"** ማለት ከቀረጥ እና ታክስ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ነፃ ሆነው በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ለቱሪስት መገልገያነት ወይም ለባህል ልውውጥ ወደ አገር በሚገቡ ሰዎች አማካኝነት የሚገቡና በጉምሩክ አዋጅ መሠረት በተወሰነላቸው የጊዜ ገደብ በገቡበት ሁኔታ ተመልሰው የሚወጡ ዕቃዎች ናቸው፡፡

3. **"የንግድ መጠን እና የንግድ ባህሪ የሌለው ዕቃ"** ማለት ከግል ወይም ከቤተሰብ ፍጆታ የማያልፍ፤ በሽያጭ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ የማይተላለፍ እና ለንግድ የማይውል የፍጆታ ወይም የመገልገያ ዕቃ ማለት ነው፡፡

4. **"ተሽከርካሪ"** ማለት በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀሱ አውቶሞቢሎች እና ሞተር ብስክሌቶች ሲሆኑ በቱሪስት ስም የተመዘገቡ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር በጊዜያዊነት ሊቀርብባቸው የሚችሉና በባህል ፌስቲቫሎች ለመሳተፍ የሚገቡ ሰዎች የሚያስገቧቸው የእንግዶች መገልገያ ተሽከርካሪዎችን ይጨምራል፡፡

5. ሌሎች በመመሪያው የተካተቱ ቃላቶችና ሐረጎች የአዋጁን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ከቱሪዝምና ከባህል ልውውጥ ጋር በተያያዘ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች እና እነዚህኑ ዕቃዎች በሚያስገቡት ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ከቱሪዝምና ከባህል ልውውጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ዕቃዎች በጊዜያዊነት የሚያስገባ ቱሪስት መብትና ግዴታ

## 4. መብት

1. ማንኛውም ነዋሪነቱ ከኢትዮጵያ ውጭ የሆነ ቱሪስት በህግ የተፈቀዱ ዕቃዎችን ማስገባት ይችላል፡፡

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ወይም ሌላ ሥራ የሚሠራ ወይም ለመስራት የተፈቀደለት ሰው ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሆነ ይገመታል፡፡

3. በህግ የተፈቀደውን የ6 ወር የጊዜ ገደብ ማራዘም የፈለገ ቱሪስት ተጨማሪ ጊዜ ለማራዘም በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 55/4 መሠረት ጥያቄውን በባለሥልጣኑ መ/ቤት የድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት ወይም በቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ወይም በመቅረጫ ጣቢያ ሥራ አስኪያጅ ታይቶ በቂ ምክንያት መኖሩ ሲረጋገጥና ተቀባይነት ሲያገኝ የመቆያ ጊዜው ከ2 ወር ሳልበለጠ ጊዜ ሊራዘም ይችላል፡፡

4. ለቱሪዝምና ባህል ልውውጥ በጊዜያዊነት ዕቃዎችን የሚያስገባ ቱሪስት እንደማንኛውም ተጓዥ በህጉ መሠረት የተፈቀደለትን የንግድ መጠንና ባህሪ የሌለው ዕቃ ይዞ የመግባት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

5. የሚወጣበትን ጣቢያ መቀየር የፈለገ ቱሪስት አስቀድሞ ለዋና መ/ቤት ወይም ለቅ/ጽ/ቤት ወይም ለገባበት ጣቢያ በማሳወቅ ፈቃድ ማግኘት ይችላል፡፡

## 5. ግዴታ

1. ማንኛውም ዕቃ ይዞ ወደ አገር የሚገባ ቱሪስት በመግቢያ ጣቢያ ዲክላሬሽን መሙላት እና የመግቢያ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ፈቃዱንም በሚዘዋወርበት ቦታ ይዞ የመገኘት እና ሲጠየቅም የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

2. ዕቃዎችን ማስገባት የተፈቀደለት ማንኛውም ቱሪስት በአዋጁ መሠረት በበቂ ምክንያት ካልተራዘመለት በስተቀር በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃውን በመጣበት ሁኔታ የማስወጣት ግዴታ አለበት፡፡

3. ዕቃ የሚያስገባ ቱሪስት በዚህ መመሪያ በተወሰነው ዓይነት ዋስትና ማቅረብ አለበት፡፡

4. ተሽከርካሪን የሚያስገባ ማንኛውም ቱሪስት የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ መያዝ አለበት፡፡ አስገቢው ተሽከርካሪውን ይዞ በተገኘበት ቦታ ሁሉ ሰነዱን ይዞ የመገኘት እንዲሁም ከዲክላራሲዮን እና ከሌሎች ሰነዶች ጋር

ማገናዘብ እንዲቻል የውጭ ሀገር ነዋሪ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ፖስፖርት፣ የመኖሪያ ፈቃድ፣ ወይም የመሳሰሉትን ሰነዶች መያዝ እና በህግ አስከባሪዎች ሲጠየቅም የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

5. ዕቃ የሚያስገባ ቱሪስት በመግቢያ ጣቢያ የሚወጣበትን ጣቢያ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ይህንን ባላደረገበት ጊዜ ሁሉ በገባበት ጣቢያ እንደሚወጣ ተደርጐ ይገመታል፡፡

6. የመንገዣ ዘዴ ቀይረው የሚወጡ ቱሪስቶች ወደ አገር ውስጥ ይዘውት የገቡት ተሽከርካሪ ተጭኖ ወይም እየተነዳ ከአገር እንዲወጣ ከፈለጉ ስለሁኔታው ለባለሥልጣኑ መ/ቤት በማሳወቅ ህጋዊ ውክልና በተሰጠው የጉምሩክ አስተላላፊ አማካኝነት ወይም በአስገቢው ተሽከርካሪው የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተፈፅሞበት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆኖ ከአገር እንዲወጣ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

7. ተሽከርካሪን ጨምሮ ቱሪስቱ ባስገባቸው ዕቃዎች ላይ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ጉዳት ሲደርስ በአቅራቢያው ለሚገኝ የትራፊክ ፓሊስ፣ ፓሊስ ጣቢያ፣ የጉምሩክ ጣቢያ ወይም አስተዳደር ጽ/ቤት ሪፓርት በማድረግ የፅሁፍ ማስረጃ ለሚመለከተው የጉምሩክ ጣቢያ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ለዋና መ/ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

8. በተሽከርካሪው ላይ ጉዳት ደርሶበት በጥገና ሊስተካከል የማይችልና መቀየር የሚኖርባቸው ከሆነ ጉዳት በደረሰበት የተሽከርካሪው አካል በምትክ የሚገዛው የተሽከርካሪው ክፍል ከብር 5,000 /አምስት ሺ/ በላይ ዋጋ የሚያወጣ ከሆነ ግዥውን ለመፈፀም ከባለሥልጣኑ መ/ቤት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

9. ቱሪስቱ በሀገር ውስጥ ለመቆየት የተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ከማብቃቱ በፊት በመውጫ በር በሚገኝ የጉምሩክ ጽ/ቤት በመቅረብ የመውጫ ፈቃድ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

10. ማንኛውም ዕቃ ይዞ የገባ ቱሪስት ከአገር ሲወጣ በጉምሩክ መውጫ በሮች ዲክላሬሽን ማሳየት ይኖርበታል፡፡

11. ለቱሪዝም አገልግሎት የሚውሉና ተመልሰው የሚወጡ ዕቃዎችን የያዘ ቱሪስት ከባለሥልጣኑ ለዚሁ ሲባል በተዘጋጀ ሰነድ ላይ በፅሁፍ የዋስትና ግዴታ መግባት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ኃላፊነት

### 6. የጉምሩክ ጣቢያዎች ኃላፊነት

1. የጉምሩክ መግቢያና መውጫ በሮች ማንኛውም ቱሪስት በጊዜያዊነት የሚገባ ዕቃ ከያዘ ዲክላሬሽን እንዲሞላ እና ተገቢው ሥነ ሥርዓት እንዲፈፀም ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

2. በመግቢያ በር የሚገኘው የጉምሩክ ጽ/ቤት ቱሪስቱ በዲክላሬሽን የሞላው መረጃ ትክክለኛነት ከኦሪጅናል ሰነዶችና በአካላዊ ዕይታ በማመሳከር ዕቃውን ለማስገባት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች መሟላታቸውን አረጋግጦ በቅፁ ለፅህፈት ቤት አገልግሎት በተወሰነው ቦታ ላይ መስፈር ያለባቸውን ማረጋገጫዎች ያሰፍራል፡፡

3. ቱሪስቱ በመጀመሪያ በገባበት በር እና ጊዜ ዕቃ ይዞ ያልገባና ዕቃው በሌላ በር ወይም በተመሳሳይ በር በሌላ ጊዜ የመጣ ከሆነ ዕቃው የገባበት የጉምሩክ ጽ/ቤት ቱሪስቱ ሲገባ ዕቃ እንደሌለው ዲክሌር ያደረገበትን ዲክላሬሽን ተቀብሎ በአዲስ ዲክላሬሽን መረጃዎችን በማወራረስ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

4. ተሽከርካሪ ጥገና ለማድረግ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች፣ መለዋወጫዎች፣ቅያሬ ጐማና ከተሽከርካሪው የነዳጅ መያዣ ታንከር ውጪ በትርፍነት /በሪዘርቭነት/ የተያዘ ነዳጅ እና የመሳሰሉት ዲክላሬሽን ላይ ሊሞላ ይገባል፡፡ ከተሽከርካሪው መደበኛ ሥሪት ይዘት ውጪ ለጌጥ ወይም ለተጨማሪ አገልግሎት የተገጠመ አካል ካለና ከፍተኛ ዋጋ ያለው ወይም ዕቃ ለመደበቅ ሊውል ይችላል ተብሎ ከተገመተ በመግለጫ ቦታ ለይ መገለፅ ይኖርበታል፡፡

5. በመውጫ በር የሚገኝ የጉምሩክ ጽህፈት ቤትም ቱሪስቱ በመግቢያ ጉምሩክ ጽህፈት ቤት የተሰጠውን የገቢ ቱሪስት ዕቃ ዲክላሬሽን ሲያቀርብ ቱሪስቱ ይዞ የሚወጣውን ዕቃ እና የባለቤትነት/የውክልና ማስረጃ ትክክለኛነት በዲክላሬሽን ላይ ከሠፈሩ

መረጃዎች/መግለጫዎች ጋር እንዲሁም ሌሎች ማስረጃዎች ጋር በማመሳከር እና ትክክለኛነቱን ከቱሪስቱ ዲክላሬሽን ላይ ለመውጫ የጉምሩክ በር ጽ/ቤት አገልግሎት በተመለከተው ቦታ ላይ በማረጋገጥ ቱሪስቱ ወይም ወኪሉ ዕቃዎቹን ይዞ እንዲወጣ ይፈቅዳል፤ ዲክላሬሽኑንም በመቀበል ኦዲት እስኪደረግ ድረስ በጽህፈት ቤት ፋይል አድርጐ ይይዛል፡፡

6. ቱሪስቱ በአገር ውስጥ ለገዛቸው የግል መገልገያና የተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤት ፈቃድ ለሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች የመውጫ በር የጉምሩክ ጽህፈት ቤት ፈቃድ መቅረቡን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
7. ቱሪስቱ ወደ አገር ሲገባ ይዞ የገባቸው በጉዞ የሚጠቀምባቸውን እንደ ነዳጅ ያሉ ምርቶች ዲክሌር እንዲደረግ በንዑስ አንቀፅ 6/4/ ላይ ከተጠቀሰው በላይ አለመያዙን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ መጠኑ በተሽከርካሪው የነደጅ መያዣ/ታንከር/ ያለውን አይጨምርም፡፡

## 7. <u>የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት</u>

1. ዳይሬክቶሬቱ ራሱ የሚያስተናግዳቸውን ጉዳዮች በዚሁ መመሪያ በአንቀፅ 8 በተጠቀሱት መሠረት ይፈፅማል፡፡
2. በራሱ የሰጠውን አገልግሎት በአባሪ በተያያዘው ቅፅ መሠረት በኮምፒዩተር መዝግቦ ይይዛል፡፡
3. ከመግቢያና መውጫ በሮች የሚደርሱትን መረጃዎች እንዲሁም በራሱ በኩል የሰጣቸውን አገልግሎቶች በማጠቃለል በመግቢያና መውጫ በሮች በሚገኙ ፅህፈት ቤቶች በየወሩ ያሰራጫል፡፡ ጽህፈት ቤቶቹም በዚሁ መሠረት በጣቢያቸው ገብተው በሌላ በር የወጡ ሽከርካሪዎችን ፋይል ይዘጋሉ፡፡ በተፈቀደላቸው የጊዜ ገደብ ያልወጡትን ተሽከርካሪዎች በተመለከተ በየ10 ቀኑ በማጣራት ለባለሥልጣኑ የህግ ማስከበር ዘርፍ፣ ለትራፊክ ጽ/ቤት እና ለመንገድ ትራንስፓርት ባለሥልጣን ክትትል እንዲያደርጉባቸው መረጃ ያስተላልፋል፡፡

4. በዚህ መመሪያ የተመለከቱና ለቱሪስቱ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ድረ ገፅ እንዲካተት ይደረጋል፡፡

## 8. የመረጃ አያያዝ ልውውጥና ስርጭት

1. የጉምሩክ መግቢያና መውጫ በሮች በሥራ ሂደታቸው በኩል መስተንግዶ ስለተሰጠው ቱሪስት ከዚህ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው ቅፅ መሠረት ዝርዝር መረጃ መስተንግዶ በተሰጠ ማግስት ባለ የሥራ ቀን ለባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል፡፡

2. የጉምሩክ መግቢያና መውጫ በሮች በክፍላቸው በኩል ለቱሪስቱ መስተንግዶ የሰጡባቸውን የገቢና ወጪ ቀሪ ዲክላሬሽን እየመዘገቡ ፋይል አድርገው ይይዛሉ፡፡

3. ስለሰጡት አገልግሎት በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በሚተላለፍላቸው ቅፅ መሠረት በወቅቱ በመመዝገብ መርሃዊ ማጠቃለያ ሪፓርቱን ወሩ ባለቀ በቀጣይ የሥራ ቀን በፋክስ ለባለሥልጣኑ የድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት ያስተላልፋሉ፡፡

4. ይህ መመሪያ ተፈፃሚ መሆን ከሚጀምርበት ጊዜ ጀምሮ የሚሰጥ አገልግሎት በእያንዳንዱ የመግቢያ በር የራሱ የሆነ ተከታታይ መለያ ቁጥር ያለው የፈቃድ ወረቀት ይሰጣል፡፡ መለያውም ሦስት ክፍሎች ይኖሩታል እነዚህም፤

   (ሀ) የመግቢያ በሩ ስም፤

   (ለ) ተከታታይ ቁጥር፣ እ.ኤ.አ. ቀመር መሠረት በዓመቱ በመጀመሪያ ለገባው ተሽከርካሪ 00001 ጀምሮ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ተከታታይ ቁጥር ይሰጣል፡፡

   (ሐ) ዓመተ ምህረት ሲሆን ይዘቱ መግቢያ በር /00001/ ዓ.ም. ይሆናል፡፡

ለምሳሌ፣ በሞያሌ በ2009 በመጀመሪያ ለሚስተናገድ ተሽከርካሪ የሚሰጠው መለያ MOY00001/2009 ይሆናል፡፡

## 9. ቁጥጥርና ክትትል

1. በመተላለፊያ መስመሮች ላይ የሚገኙ የጉምሩክ ጣቢያዎች በተለያዩ ምክንያቶች ክትትል እንዲደረግባቸው መረጃ በተላለፈባቸው ዕቃዎች ላይ ቁጥጥር በማድረግ ዕቃውን መረጃውን ላስተላለፈው ክፍል ወዲያውኑ ውጤቱን ያሳውቃል፤ እንደአስፈላጊነቱም በአጃቢ ለጠያቂው ክፍል ያስተላልፋል፡፡

2. የተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤት ፈቃድ የሚያስፈልጋቸውን ዕቃዎች ቱሪስቱ ይዞ በመምጣቱ በመግቢያ በሮች ላይ ፈቃድ መስጠት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ የመግቢያ በሩ ጣቢያ ዕቃዎቹን በአጃቢ ፈቃድ ወደሚሰጥበት አካባቢ ለሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ በማስተላለፍ ፈቃድ ሲገኝ ዕቃው እንዲለቀቅ ያደርጋል፡፡

## 10. በተወሰነው የጊዜ ገደብ ስላልተመለሰ ዕቃ

በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 55/1/ ወይም 55/4/ መሠረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ወይም በተራዘመለት ጊዜ ውስጥ ዕቃው ተመልሶ ካልወጣ የአዋጁ አንቀፅ 55/5/ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 11. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጐች

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 12. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመፅናቱ በፊት ተጀምረው እልባት ወይም ውሳኔ ያላገኙ በመመሪያው ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት ውሳኔ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

## 13. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ………………ቀን 2003 ዓ.ም.**

**መላኩ ፈንታ**

**የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**